ኢትዮሚዲያ

# ከፕሮፌሰር አቢጌል ሳሊስበሪ ጋር ያደረገው መጠይቅ

ትርጉም መላኩ ፀጋዬ መኮንን

*የአዘጋጁ ማስታወሻ* ፤ አብዛኛዎቹ የኢትዮሚዲያ አንባቢያን የሕግ ባለሙያና መምህርት አቢጌል ሳሊስበሪ፤ ጁሪስቲን ኦን ላይን ከተባለው መጽሄት ጋር ስለመቀሌ ዩንቨርስቲ የትምህርት ነጻነትና በሰብአዊ መብት ረቂቅ ድንጋጌ (**HR 2003**) አስመልክቶ በጻፉት መጣጥፍ ያውቋቸዋል።ፕሮፌሰር አቢጌል በዩንቨርስቲው በማስተማር ላይ በነበሩበት ወቅት ስለገጠማቸው ጉዳይና በዚሁ የተነሳ ከስራ ስለመሰናበታቸው ኢትዮሚዲያ በዝርዝር ቃለመጠይቅ አድርጎላቸዋል።

*አብርሃ በላይ* : ፕሮፌሰር አቢጌል ሳሊስበሪ ይህን ቃለ መጠይቅ ለመስጠት ስለተባበሩኝ አመሰግናለሁ፤በጣምም እናመሰግናለን።በቅድሚያ በመጋቢት ወር **2000** ዓ. ም የአሜሪካ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር በኢትዮጵያ ስለአለው የትምህርት ነጻነት ስለሰጠው አስተያየት ልጠይቀወት "መንግሥት በዚህ አመት የመማር ነጻነትን ገድቧል፤መምህራን ስለፖለቲካ አስተያየት መስጠት አይፈቅድላቸውም።ባለስልጣናት ስለትምህርት አሰጣጥ መነጋገር እንዳይቻል ከልክለዋል።ስለፖለቲካ በዩንቨርስቲው ግቢ እንዳይነሳ የተከለከለ ሲሆን በግቢው በማንኛውም መልኩ በማህበር መደራጀትም ክልክል ነው" ይላል ይህን መግለጫ ይስማሙበታል ወይስ ይቃወማሉ፤ቢያንስ ሲያስተምሩበት ስለነበረው የመቀሌ ዩንቨርስቲ?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ስለሰጠው ማጠቃለያ ሙሉ በሙሉ እስማማለሁ። መግለጫው በእኔ ልምድ ብቻ ሳይሆን ከሌሎችም ባገኘሁት መረጃ ጭምር ትክክል ነው። ሌላ ለረጅም አመታት በኢትዮጵያ ያስተማረች አሜሪካዊት እንደነገረችኝ የፋካሊቲው የማስተማር መርሀ ግብር አውጥቶ የሰጣት መሆኑንና የተሰጠውን የማስተማሪያ እቅድ ተከትላ ለማስተማር የተከለከተች መሆኑን ነግራኛለች፡ እኔም የተሰጠኝ መመሪያ በኢትዮጵያዊ መምህር በተዘጋጀ ማስተማሪያ መፅሐፍ መሰረት እንዳስተምር ነው።ከዚህ በተጨማሪ እኔም ከነበረኝ የማስተማር ልምዴ ባገኘሁት ምሳሌዎችን እጠቀም ነበር። በጂሪት መጣጥፌ ላይ እንደገለፀኩት የመምህርነት ውሌ ላይ ምንም አይነት የፓለቲካ ነክ አስተያየት ነገር እንዳልጠቀም ይገድበኛል።

*አብርሃ በላይ* : በመላ ዓለም የማስተማር ነፃነት የከፍተኛ ተቋማት መሰረት እንዳሆነ ይታመናል፤ በተለይም በአሜሪካ፤ ምክንያቱም ለተማሪዎችም ሆነ ለመምህራን ሁሉ አቀፍ የሆነ እውቀት እንዲኖር ያለምንም ፍራቻና የመንግስት ብቀላ የማስተማር ነፃነትን ይጠቀማሉ፡ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ በነበሩበት ወቅት የማስተማር ነፃነትን በተመለከተ ስለአለው ሁኔታ ሊያብራሩልን ይችላሉ? እንደዚሁም መንግስት ''አቀንቃኝ'' የሚለውን እንዴት ነው የሚተረጉመው?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : እንደአየሁት የማስተማር ነፃነት በጣም የተገደበ ነው ። አንዱ አደጋ ተማሪዎች በተቃወሙ ቁጥር የመምህራን ከስራ መባረር አንድ የችግሩ አካል ነው። ተማረዎች በርካታ መምህራንን የማስተማር ስልታቸውን ባለመደገፋቸው የተነሳ ከስራቸው እንዲሰናበቱ የማድረግ ሀላፊነት ተለጥፏቸዋል። ተማሪዎት መምህራንን፤ በፆታቸው፤ በሀይማኖታቸው፤ በተወለዱበት አካባቢና በመሳሰሉት ጉዳዮች ላይ በማተኮር ተደጋጋሚ የተቃውሞ ፊርማ ያሰባስቡባቸዋል። የዩኒቨርሲቲው አስተዳዳሪ ተማሪዎች በአንድ መምህር ላይ የሀሰት ውንጀላ ሊያሰሙ እንዲይችሉ ለማድረግ ባንድ ወቅት የማስተምርበት ክፍል ትምህርት ለ**30** ደቂቃ እንዲቋረጥ ተደርጎ ነበር። አንዲት መምህሪት ከተማሪዎች ፊት ለመቆም በመቸገሯ መበጨረሻ ማስተማር ማቆም ተገደደች። ተማሪዎች ስርዓት አልባ እየሆኑ በመምጣታቸው እና መምህራንን ከመቆጣጠራቸው የተነሳ ለዲኑና ለምክትሉ ይህ እንዲስተካከል አመልክቸ ነበር። ተማሪዎች በተደጋጋሚ ለገንዘብ ልመና ወይም ለማዋከብ የአስተማሪዎችን ቢሮ ይመላለሱበታል።አስተማሪዎች በማስተማሪያ ቢሮአቸው አያዘወትሩም። በእንደዚህ አይነት ተጨባጭ ሁኔታ የተነሳ ስጋትና ጥላቻ አለ። ስለሆነም የሚያበረታታ ተጨባጭ ሀሳብ ማመንጨት አይቻልም፡ ምንም አይነት የፓለቲካ ሁኔታ ቢከሰት መነጋገር አይቻልም፤ በበኩሌ መንግስት ማቀንቀን የሚለውን ቃል እንዴት እንደሚተረጉመው አላውቅም በተግባር ትርጉሙ ስለተለያዩ አስተሳሰቦችና ተቃውሞዎች ገንቢ ሀሳብ መግለፅ ነው ምን አልባት ትርጉሙ ሆነ ተብሎ የተለዩ ትርጉሞች እንዲኖረው የታለፈ ሊሆን ይችላል።

*አብርሀ በላይ* ፡ በርካታ ኢትዮጵያውያ የውጭ ሀገር መምህራን እንዴት እንደሚቀጠሩ ኢያውቁም። እንዴት ተቀጠሩ፤ ሲቀጠሩስ የታዋዋሉበት ሁኔታ ምን ነበር?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡ በየአመቱ በኢትዮጵያ የሕግ ት/ቤት እንዳያስተምሩ መምህራንን የሚመለምል አሜሪካዊ ፕሮፌሰር አለ።

የእኔን የስራ ማመልከቻ ለእርሱ ላኩት ምክንያቱም ከጥቂት አመት በፊት ፒት የሕግ መምህር የነበረ መቀሌ ዩንቨርስቲ እንዲያስተምር መደረጉን አውቄአለሁ፡ ስራውንም አደንቀዋለሁ፡ ባለፈው አመት ረዳት ፕሮፌሰር እንድሆንና የማስተምርባቸው ሁለት ከተሞች ምርጫ ተሰጥቀውኝ ነበር አዲስ አበባና መቀሌ ነበሩ።ነገር ግን አ፡አ ዋና መናገሻ ስለነበርና መቀሌ የሚያስተምር መምህር ስለማውቅ መቀሌ ማስተማሩን መረጥኩ ።በዚሁ መሰረት መቀሌ ተመደብኩ፤ ሆኖም የትኛውን የትምህርት አይነት ማስተማር እንዳለብኝ ግን አልተነገረኝም። በዚሁ ምክንያት በርካታ የማስተማሪያ መረጃዎችን አሰባስቤ ሄድኩ። እንደኔ በተመሳሳይ ሂደት ሰባት ሌሎች መምህራን ከአሜሪካ ወደ ኢትዮጵያ ተልከው ነበር። መጀመሪያ መጠነኛ መረጃ ነበር የተነገረኝ። ከሄድኩ በኃላ ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማጣራት ነበረብኝ፤ እንደኔ ግምት ከሌሎች መምህራን ጋር የመኖሪያ ቤት ይሰጡኛል የሚል እምነት ነበረኝ። መቀሌ ስደርስ ግን በዩኒቨርስቲው ብቸኛ አሜሪካዊት መምህር እኔ ብቻ ነኝ። በመሆኑም መኖሪያየን በግሌ መፈለግ ነበረብኝ። በመቀጠልም ትምህርቱ ከመጀመሩ ቀደም ብሎ አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ሕግን እንዳስተምር ተመደብኩ፡ የስራ ውሌን ሳልፈርም በርካታ ሳምንታት አለፉ፤ በተለይም በጣም አስፈላጊ የነበረውን ማናኛውንም ፓለቲካ አመለካከት እንዳላራምድ /እንዳላቀነቅን/ የሚጠይቀውን የግዴታ ውል ማለት ነው። የሕግ ትምህርት ቤቱ የአሜሪካ ፕሮፌሰሮች እንዲያስተምሩበት የተዘጋጀ አልነበረም። አንድ መምህርት ምንም ሳይከፈለው ወይም ወጭው ሳይመለሰለት እንዲለቅ ተደርጓል። ከዚያም ሁለት አሜሪካዊ መምህራን ስራቸውን ጥለው ወደ አሜሪካ መመለሳቸውንም በመጨረሻ ሰማሁ። ከሕንድ እንደዚህ መምህራን አሉ። የተቀጠሩት በተለያየ መርሀ ግብር ነው /ፕሮግራም/ ይህም ከአሜሪካኖች በተሻለ ስለጉዳዩ እንዲያስቡበት ጊዜ ነበራቸው።

*አብርሃ በላይ* ፡ ስለማስተማር ነፃነት ጉዳይ ልመለስ ይህ በአሜሪካ ዩኒበርስቲዎች የሞቀ ውይይት የሚደረግበት ጉዳይ ይመስላል፤ የዩኒቨርስቲ ፕሮፌሰሮች የሚነጋገሩት ስለማስተማር ነፃነት ብቻ ሳይሆን ስለ ሕዝባዊ ፓሊሴዎች ጭምር ይወያያሉ። በአሜሪካ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ካለወትም ልምዶች ጋር በማነፃፀር በዚህ የስራ ምደባ ምን ተሰማዎት?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡- የአሜሪካና የኢትዮጵያ ዩኒቨርስቲ ካሪክለም /የማስተማሪያ ስርዓት/ ብዙ ልዩነት ሊኖረው አይገባም። በአጠቃላይ በአሜሪካ ከፍተኛ ትምህርት በተለይም በሕግ ትምህርት ዘርፍተማሪዎች በሚማሩበት ጊዜ ሀላፊነትን እንዲወስዱ ይደረጋል። በተለያዩ ወሳኝ ጉዳዮች ላይ እንዲሳተፉ ይመደባሉ። የክፍል ውይይት ይካሄዳል። ትምህርት በመቀሌ የሕግ ት/ቤት የተጀመረ እለት ተማሪዎችን ስማቸውን እንዲያስተዋውቁና በሰብአዊ መብት ጉዳይ ያደረባቸውን ፍላጎት እንዲገልፁ ጠየቅሁ። በተለይ ተማሪውን ስሙን ወይም ስሟን መጠየቅ ተማሪው ተቀምጦ ማዶ ማዶ ማየት ብቻ ነው አይናገሩም፤ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የክፍል ውይይት የሚባል አላስፈላጊ መሆኑ ገባኝ፡ በጥቃቅን ነገሮች እንኳን ሳይቀር ተማሪዎች እንዲናገሩ በጣም ጣርኩ ለምሳሌ "በቀረበ ሀሳብ ላይ ማን ይስማማል? የተስማማ እጁን ያንሳ ስልማ" ዝም ብቻ ነው። " ያልተስማማ ማን ነው? እጅ አውጡ ወይም አንሱ" ማንም እጅ አያወጣም ተማሪዎቹ የሚፈልጉት ፋክት/መረጃዎችን አግኝተው እነርሱኑ ማጥናት ብቻ ነው። በቀረበ ሀሳብ ትንተና እንዲሰጡ ከተጠየቁ የግልና አስተያየታቸውን እንዲያክሉ ከተነገራቸው ይናደዳሉ። በተማሪዎቹ ፍላጎት በጣም ተገርሜ ነበር። ሁል ጊዜ በግልፅ የሚፈልጉት በዚያ መንገድ ብቻ እንዲማሩ ነው። ሌሎች የውጭ ሀገር መምህራን ተመሳሳይ ችግር እንዳለባቸው ነግረውኛል።

*አብርሃ በላይ* ፡ የስራ ውሉን ስፈራረሙ " ስለመንግስት ወይም ስለገዥው ፓርቲ በፍፁም ምንም ነገር እንዳይናገሩ" የሚል አንቀፅ አለበት፤ ስለዚሁስ ማብራሪያ ጠይቀው ነበር?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡ በስራ ውሉ ላይ ይህን አንቀፅ በማየቴ አስደንቆኝ ነበር ነገር ግን እኔ የማደረገው ምንም ነገር አልነበረም በዩኒበቨርስቲው የሆነ ሰው ለድርድር እንዳይቀርብ አድርጎ በስራ ውሉ ላይ አስሮ አስቀምጦታል። ይህንን ምንም ወደ ዳኒ ለመወሰድ አልፈለኩም ምክንያቱም ስራ ከመጀመሬ ችግር ፈጣሪ ተብዬ መመደብን አልመረጥኩትም ነበር።

*አብርሃ በላይ* :_ባለፈው ቃለ መጠይቅ ላይ እንደገለፁት በጂረሲቲን አን ላየን በፃፉት መጣጥፉ የተነሳ ከስራወ መሰረዘወትን ገልፀው ነበር ማን ነበር መሰናበተወን የነገረወ? በምንስ ምክንያት ነው የተሰናበቱት አሉ?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : መጣጥፌ በወጣ ማግስት ኢትዮጵያ ሆኖ መስመር እንደማይገኝ ተገንዝቤ ነበር፤ ማታ ወደ አንድ ሰዓት ገደማ ከሕግ ተቋሙ ዲን ስልክ ተደወለልኝ፤ ከዚያም በሚቀጥለው ቀን ጧት ቢሮ እንድገኝ ተነገረኝ።ስለተጠራሁበት ጉዳይ ምንም ማብራሪያ አልተሰጠኝም በማግስቱ ዲኑንና ሁለት የተቋሙ መሪዎች በቢሮው ሁነው ተገናኘን። በመቀጠልም ተማሪዎቹ ምንም እንዳልተማሩ በመግለፅ አቤቱታና ቅሬታ ስለአቀረቡ ሚስጥራዊ ማጣራት ተጀምሮብሻል አሉኝ።እኔ ቀደም ብዬ ተማሪዎቹ ለወራት ትምህርት እየተከታተሉ አለመሆናቸውን፤ የምስጣቸው የሚነበቡ ጽሁፎች "ከአቅማቸው በላይ " መሆኑን ከዚህም ሌላ አስቸጋሪ ባህሪ እንዳለባቸው ተናግሬአለሁ። ተማሪዎቹ በእኔ ላይ ያፈጡብኛል፤ ከክፍል ጥለው ይወጣሉ፤ እኔን ምን መስራት እንዳለብኝ ያዙኛል፤ ገንዘብ ይጠይቁኛል፤ ቤቴ ድረስ ይከታተሉኛል፤ በቢሮ ሰዓት በወሲብ ጉዳይ ያዋከቡኛል፤ እኔም ለዲኒ እና ለምክትሉ ብሎም ተሰሚነት ላላቸው ነባር ፕሮፌሰሮች ለበርካታ ጊዜ ምክር ጠይቄአለሁ፡ ሆኖም ምንም ሊያግዙኝና ሊረዱኝ አልቻሉም። ዲኑ ከስራ ለምን እባረራለሁ ብለሽ ደብዳቤ ፃፊ አለኝ፡ የሆነ ሆኖ ከሳሾቹን በግንባር ሊያቀርቡአቸው ግን አልቻሉም።

*አብርሃ በላይ* :- እርሰዎ እንደሚሉት ከሳሾቹን ለመከራከርና ጉዳዩን በመረጃ ለማቅረብ ለመከላከል የሚያስችል እድል በትንሹም እንኳ ቢሆን አልተሰጠወትም፤ ይህ ለሕግ ሰው በጣም ከባድ ነገር ነው። ኢትዮጵያውያን ይህን የመከላከል እድል ያገኛሉ? የሚገርመኝ የሕግ ባለሙያና የሕግ ፕሮፌሰር ይህ እድል ሲነፈግወ እና በጣም መሰረታዊ የሕግ ስርዓት ሲጣስና ይህ የሰብአዊ መብቶች ሁሉ መሰረት የሆነው የመከላከል መብት ሲነፈገወ የተሰማወት ስሜት ምን ነበር?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : አንድ ተማሪ በተደጋጋሚ እኔንና አንድ መምህርት መብታችን ሲተላለፍ ዲኑ የነገረኝ ተማሪውን ከዩንቨርስቲው ሊያባርረው እንደማይችል ነው። ለምን ቢባል አቤት የማለትና ጉዳዩን ለሌላ የበላይ አካል የማቅረብ መብት እንዳለው አስረዳኝ። በተደጋጋሚ የአበሳለጨኝ ጉዳይ በክፍል የምናስተማረው ፅንስ ሀሳብ እንጂ በተግባር ላይ የሚወል ፍሬ ነገረ አለመሆኑ ነው።

*አብርሃ በላይ* : የመንግስት ይዞታ በሆነው የሕትመት ውጤት እርሰዎ ከስራወ የተባረሩት "በችሎታ" ማነስ ነው ተብሏል። ይህ ክስ የተነሳው በጅሪስት የእርሰዎ፡ መጣጥፍ ከወጣ በኃላ ነው። የእርስዎን ጽሁፍ ያነበቡ በብዛት የሚሉት የእርሰዎ ከስራ መስናበት ከፃፉት መጣጥፍ ጋር በተያያዘ ለመበቀል የተወሰደ እርምጃ ነው ብለው ያምናሉ፡ የእርሰዎ ከስራው ተየሰናበቱበት ድብዳቤ ይህንኑ በግልፅ ያስረዳል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : ቀደም ሲል ዲኑና ሌሎች የዩኒቨርስቲው አመራሮች በግል መቀሌ ቆይቼ የመማሪያ መፃህፍት እንድሰራ ጠይቀውኝ ነበር። ከሁለት ቀናት በኃላ ግን የእኔ ጉዳይ "ታይቶ" የስራ ውሌ ተቆርጦ እንድስናበት መወሰኑን ነገሩኝ። የእኔ ጉዳይ ሲነሳ በአካል ተገኝቼ እንኳ እንድሰማ አልተፈቀደልኝም፤ እነማን ጉዳዩን እንደተነጋገሩበትም አላውቅም። በግልፅ መሰናበቴን የሚገልፅ ደብዳቤም አልደረሰኝም። አንደ መረጃ ያገኘሁት፤ ለገንዘብ ከፋይ መስሪያ ቤታቸው ከስራ የተሰናበቱ ስለሆነ ያለፈ ወር ደመወዝ እንዲከፈላቸው የሚል ትእዛዝ ነው። እኔ "ብቃት የላትም" የሚለውን አባባል መስማት የጀመርኩት በስራ ውሌ መሰረት ስራው ሲቋረጥ የሶስት ወራት የአገልግሎት ክፍያ ገንዘብ ስጠይቅ ነው። የዩኒቨርስቲው ባለስልጣናትም ገንዘቡን ሊከፍሉኝ እንደማይችሉ፤ ምክንያቱም የተሰናበትኩት "በችሎታ" ማነስ መሆኑን አረዱኝ። ይህ አንቀፅ በዚህ ጉዳይ ላይ ተግባራዊ የሚሆን አይደለም። በስራ ውሌም ላይ ይህ ነገር የለም። በጣም ያስገረመኝ ነገር "በችሎታ" ማነስ መወንጀሌ ነው ከዲኑ ከራሱ ብዙ አመታት የትምህርት ብልጫ ያለኝ መሆኑ ግልፅ ነው። ዲኑ የጁሪስት መጣጥፌን አንስቶም የሰፈረው ሀሳብ በሙሉ ውሸት ነው፤ በዚህም መፃፍ አለመቻሌን ያረጋገጠ ነው፤ እንዴት መፃፍ እንደምችል ባውቅበት ኑሮ፤ ነገሮች ሁሉ ይለወጡ ነበር ብሎኛል።

*አብርሃ በላይ*: የተቋሙ አባላት የሆኑ ኢትዮጵያውያን እርስዎን ለመደገፍ የሞከሩ ነበሩ? ወይስ በግል የሰሩት ስራ ትክክል ነው። ግን በአደባባይ ለመናገር ፈራን ሲሉ የገለፁ ነበሩ?

*አቤጌል ሳሊስበሪ :* ሁሉም ነገር የተፈፀመው በጣም በፈጠነ ሁኔታ ነው፡ ከውጭ ሀገር ለመምህርነት ከመጡ ማህበራዊ ቡድን ውጭ ሌሎች መምህራን ምን እንደተፈጠረ አያውቁም። ከሚከተለው ችግር ለማምለጥ በተቻለ ፍጥነት ሀገሪቱን ለቅቄ እንድወጣ አሜሪካኖች መከሩኝ። በመሆኑም ማንንም ለመሰናበት እድል አልነበረኝም። ያደረኩት ነገር ቢኖር የአማረኛ ቋንቋ መምህሬን ጠርቼ፤ የምግብ ማብሰያ ቁሳቁሶቹን ስጠሁት። አንድ ኢትዮጵያዊት ወዳጅን መምህርት ደግሞ የቤቴን ቁልፍ ወሰዳ ሰፋውን እንድትወስደው ነግሬአለሁ። እርሷም ምን እንደተፈጠረ የምታውቀው ነገር እንደሌለ ነገረችኝ። የተማሪዎች ቅሬታም ሆነ ሌላ የተነገረ ነገር አለመኖሩንም ጠቀሰችልኝ። በሚቀጥለው ቀን መቀሌን ለቅቄ ወጣሁ። አሜሪካ ከመመለሴ በፊት በአዲስ አበባ ከተማ ከጓደኞቼ ጋር ጥቂት ቀናት ቆይቻለሁ።

*አብርሃ በላይ*_:- በመቀሌም ሆነ በሌሎች የሀገሪቱ ዩኔቨርስቲዎች የሚኖሩ የአሜሪካ መምህራን እርሰዎን በመደገፍ ሀሳባቸውን በግል የገለፁ ነበሩ? የእርሰዎ መባረር በእነርሱስ ላይ የሚያከትለው ተጽኖ ይኖራል ብለው ይሰጋሉን?

*አቢጌል ሳሊስበሪ :*_አሁንም ሁሉ ነገረ የተፈፀመው በጣም በፍጥነት ነው። ማንም በጉዳዩ ላይ ለመነጋገረም ጊዜ አልነበረም። በሌላ የትምህርት ዘርፍ ከሚያስተምሩ የሕንድ መምህራን ጋር ጓደኞች ነበሩኝ ነገር ግን እነርሱ በጉዳዩ ውስጥ ገብተው ምንም ነገር ማለት አልፈለጉም። በምንም ሁኔታ በሌሎች ከተሞች ከሚያስተምሩ አሜሪካዊያን መምህራን ጋር ግንኙነት አልነበረኝም። ግንኙነት ቢኖረኝ ኑሮ እንኳ ምንም የሚፈይዱት ነገር አልነበረም። ተጽኖ ማድረግ የሚችሉ አሜሪካዊያን በጉዳዪ ላይ የሚመለከታቸውን ሰዎች ደውለው አነጋግረው ነበር።ሆኖም ግን የእኔ መባረር ፀና።

*አብርሃ በላይ:* አንድ በጄሪስት መጣጥፈው የገለጡት ጉዳይ የ(**HR 2003** በአሜሪካ የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ይዞታ ረቂቅ ሕግ) ነው ለኢትዮጵያ የሚጠቅም ነገር ነው ብለው ያምናሉ? ከሆነስ ለምን?

*አቢጌል ሳሊስበሪ:-* የእኔ መጠጥፍ ስለ ረቂቅ ደንቡ አሁን ያለኝን አመለካከት እንዴት ልደርስ እንዶቻልኩ በቅደም ተከተል የዘረዘርኩበት ነው። በመጀመሪያይህ ረቂቅ ሕግ/**HR 2003**/ ጥሩ ሀሳብ አልመሰለኝም ነበር። በመጨረሻ ላይ ግን አሜሪካ ይህን አቋም መውሰድ እንዳለባት ተገነዘብኩ። ይህ ግን የኢትዮጵያን ሁኔታ ይቀይረው አይቀይረው አላውቅም። ምን አልባት ፕሮፌሰር ኖበርት ፓፐ የጥናት ጽሁፍ እንደሚለው የኢኮኖሚ ማዕቀቡ ይህን መንግስት ሊያጠናክረው ይችል ይሆናል። ነገር ግን ያለመታደል ሆኖ አሜሪካ ለራሳችን ጥቅም ስንል ከጨቋኞች ጋር እንተባበራለን። **HR 2003** ይህንን አይነት መሰረታዊ መርህ በአቋም ደረጃ እንድንቀይር የሚያደርግ ነው። ልምድ ያስተማረኝ ነገር ቢኖር ሌሎች መንግስታት በገንዘብም ሆነ በሌላ መንገድ በኢትዮጵያ ውስት ያለውን የሰብአዊ መብት ይዞታ ለመቀየር ጫና መፍጠር አለባቸው። በርካታ ሰዎች እንዳሉኝ ኢትዮጵያዊ ብሆን ኑሮ በፃፍኩት መጣጥፍ እስር ቤት እወረወር ነበር። በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጥሰትን ለመግታትና ለወጥ ለማምጣት በእርዳታ ገንዘብ አሰጣጥ ላይ ተጽእኖ ማሳደር መንግስትን ሀስቡን እንዲቀይር የሚያደርግ ጠንካራ አመለካከት ነው።

*አብርሃ በላይ:-* ማንም እንደሚገምተው ከጄሪስት መጣጥፍ መታተም በኃላ በድሁፉ ላይ ያወጡትን ትንተና የሚወዱትም ሆነ የሚጠሉት ሰዎች መልክት ይደርሰወታል፤ስለዚህ ያለወትን ሀሳብ ሊያካፍሉን ይቻላሉ?

*አቤጌል ሳሊስበሪ:-* በኢ-ሜልም ሆነ በሌላ ሰዎች ስለእኔ የሚሉት በጣም የተሳሳተ ነው። ሌላው ይቅርና ሰው መሆኔንም ሊፈታተኑ ይሻሉ። የእኔ ቤተሰቦቼና ጓደኖቸ የተለያዩ ጥቅሶችን፤ ቀልዶችንና የሚያስቁ ነገሮችን ይልኩልኛል። ምክንያቱም በሀሰት እንደተወነጀልኩ ስለሚያውቁ፤ ያልተባልኩት ነገር የለም። የኤርትራ መንግስት ሰላይ ከመባል ጀምሮ ተማሪዎቼ ፕሬዚዳንት ቡሽን ምን ያህል እንደሚወዱ በማየት የፈተና ውጤት የምስጥ መሆኑን እስሚገልፅ አባባል ድረስ አስተያየት ስጥተዋል። አሁን ስለእኔ የተፃፈን ነበር በሙሉ ማንበብ አቁሜአለሁ። ስለፃፍኩት መጣጥፍ የሚላክ ማንኛውንም ኢሜል በመሰረዝ ላይ ነኝ። የሬዲዮ ቃለመጠይቅ እንድስጥ ስጠየቅ ጉዳዮ ከጀርባው ሌላ መልክት ይኖረዋል በሚል ስጋት ለመወሰን ጥቂት ጊዜ ወስዶብኛል።

በሌላ በኩል ደግሞ ስለዚሁ ጹሁፍ በጣም የሚበረታቱ የድጋፍ መልሶችም ደርሰውኛል። የማስታውሰው "ችሎታ" የለሽም እንደተባልኩ ወዲያውኑ አንድ በዩኒቨርስቲው ግቢ የተለጠፈ ነገር አነበብኩ። ማን እንደፃፈው ባላውቅም የእርሷ ወይም የእርሱ መምህር መሆኔን እንደሚያደንቅ አነበብኩ። እንዲህ አይነት አስተያየት በጣም ስሜት የሚነካና የሚያበረታታ

ነበር። እኔንም ይበልጥ ከተፈጠረብኝ ሁኔታ ጋር በማነፃፀር እንድጠነክር አደረገኝ። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ስሜቴ እንዲረጋጋ ረዳኝ። አንዳንዶች የመሰናበቴን ሕጋዊነት እንዲገረሙ አድርጓቸዋል።

*አብርሀ በላይ*፡ ወደ ትምህርት ጥራት ልመለስ፤በተላይ በመቀሌ የሕግ ትምህርት ቤት ስለትምህርት አስጣጡ ጥራት ፤ በአጠቃላይ ደግሞ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ስለሚሰጠው የትምህርት አሰጠጥ ያለውትም አመለካከት ቢያበራሩልኝ?

*አቢጌል ሳሊስበሪ*፡ እንደ እኔ በመቀሌ የሚሰጠው ትምህርት በጣም ደረጃው ዝቅ ያለ ነው።የዩኒቨርስቲውን ምሩቃን ቀጥረው የሚያስሩ የተወሰኑ የውጭ ድርጅት አሰሪዎች ጋር ተነጋግሬአለሁ።የነገሩኝ እነዚህ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ምሩቃን ምን እንደሚስሩ የሚያውቁ አይደሉም በማለት ነው። እራሱ የዩኒቨርስቲው መምህራን ገና ወጣቶችና ምንም ልምድ የሌላቸው ናቸው። እነዚህ ለተማሪዎች በቂ እውቀት ይሰጣሉ ብየ ለመናገር ይከብደኛል። በየአመቱ አዳዲስ ዲን ይቀያየራል። ሰራተኞች ይዘዋወራሉ። እኔ እንደማውቀው የአሜሪካን መምህራን የትምህርት ደረጃና በእድሜም ከተማሪዎች የሚባልጡ ናቸው ብየ ስነግራቸው ይገረማሉ። ይህ አይነት አሰራር አሜሪካ ሀገር የማይታሰብ ነው።

*አብርሃ በላይ*፡ አንዳንድ ተማሪዎችም ሆነ ተቋሙ የእርሰዎን በትምህርት አሰጣጥ ሂደት ላይ ያለወትን አስተያየት ከማስተማር ስልተወ ጋር በማጣመር በተሳሳተ መልክ አዛምደው የተመለከቱት ይመስለዎታል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ*፡ እንደምረዳው በመባረሬ የብቀላ እርምጃ በመውሰድ የሰነዘርኩት አስተያየት ሊመስላቸው ይችላል፤ ይህ ግን አለመሆኑን ያውቃሉ፤ ለምን ለዲኑ እና ለምክትላቸው እነዚህ ችግሮች መኖራቸውን ከመሰናበቴ ቀደም ብየ ከወራቶች በፊት ነግሬአቸዋለሁ ይህን ነገር የምገፋፋበት፤ ምንም ድብቅ አጀንዳ የለኝም። በኢትዮጵያ በርካታ አሜሪካዊያን በማስተማር ታላቅ ልምድ ያላቸው መሆኑን አውቃለሁ። በመቀሌ በምንም ነገር ደስተኛ አይደለሁም። ይህም ሆኖ ለመቀሌ የሕግ ተቋም ቤተመፃህፍት መፃህፍትን በስጦታ አበርክቻለሁ። ምን አልባት ሰዎች የትምህርት አሰጣጡን ሁኔታ ችግር መኖሩን ከተረዱ እንዲሻሻል ይረዳቸው ይሆናል። በሁለታችን የተፈጠረው ችግር ብዙው ምን አልባት የማያስደንቀኝ ነገር ቢኖር በመካከላችን ባለ የባህል ልዩነት የተነሳ መረዳት ያለመቻላችን ሊሆን ይችላል።

*አብርሃ በላይ*፡ በማስተማር ላይ በነበሩበት ወቅት የእርስዎ ተማሪዎች በሕግ ትምህርት ሂደቱ ላይ ያተኮሩ ሁለት ወይም ሰባት ጉዳዮች ላይ ቅሬታ ነበራቸው ምንድን ነበሩ ቅሬታዎቹ?

*አቢጌል ሳሊስበሪ*፡ ለተማሪዎች የሚሆኑ የማስተማሪያ ቁስቁሶች አልተሟሉም፤ ትምህርቱ ሊገባቸው አለመቻሉን፤ እውነተኛ ምሳሌ በትምህርት አሰጣጡ ወቅት እንደማይፈልጉ እና ጭብጥ ነገሮችን ብቻ ማጥናት እንደሚፈልጉ ነበር የጠየቁት።

*አብርሃ በላይ*፡ በመቀሌ ዩኒቨርስቲ ያለው የሕግ ትምህርት አሰጣጥ ጋር እንዴት ያዩታል? በተለይም የመምህራንን የሕግ ጥልቅ እውቀትና ሕግ ለማስተማር ያላቸውን ብቃት?

*አቢጌል ሳሊስበሪ*፡ ሁኔታዎች እንዲቀየሩ ከተፈለገ የትምህርት አሰጣጡ ተማሪዎች የተሰጣቸውን ከመሸምደድ ወደ መተንተን ደረጃ መለወጥ አለበት። በመጀመሪያ የትምህርት አጋማሽ የተመረቀ ተማሪ በሁለተኛው የትምህርት አጋማሽ ላይ መምህር ሆኖ ይመደባል። አንድ ያገኘሁት መምህር አንድ አመት ብቻ የሕግ ትምህርት ያለው ነው። እንዲያውም የሰለጠነው በጋዜጠኝነት ሙያ ነው።ብቁ መምህራን ከማጣታቸው የተነሳ የውጭ ሀገር አስተማሪዎችን እንዲቀጥሩ ፍላጎት አሳድሮቻቸዋል። አንዳንድ ኢትዮጵያውያን መምህራን ይህ ያበሳጫቸው ይመስላል፤ ምክንያቱም የውጭ መምህራን የሚከፈላቸው ብዙ ነው። ይህን በሚገባ እገነዘባለሁ። ምክንያቱም አንድ የውጭ መምህር አሜሪካ ሀገር መጥቶ የምናስተምረው ተመሳሳይ ሆኖ በክፍያ ግን 10 እጥፍ የሚበልጠኝ ከሆነ እኔም በጣም እናደዳለሁ።

የመቀሌ ዮኒቨርስቲ ተማሪዎች በታይፕ የተፃፈ ሶስት ወይም አራት ገዶች እንዲያነቡ ስጠይቃቸው ቅሬታ አላቸው። በአብዛኛው ማንበብ የሚባል ነገር አይፈልጉም ፤አያነቡም። ሌሎች መምህራንም የነገሩኝ ተማሪዎች በጣም ዝቅተኛ ዝግጅት ያላቸው መሆኑን ነው ።የሚሰጣቸውን የቤት ስራ አይሰሩም አንዳዶቹ መፃፊያ ይዘው አይገቡም ከፊሎቹም ስከረው ይገባሉ። በየሳምንቱ መጠነኛ የሙከራ ፈተና እሰጣለሁ ።የመልስ መስጫው ወረቀት ስም፤ የተማሪው መለያ ቁጥር እና መግለጫ

ያለው ወረቀት ይሰጣቸዎል "ለእኔ በማይገባኝ ሁኔታ" ወረቀቱን መኖራቸውን ብቻ ለመግለፅ ያህል መልሰው ይሰጡኛል፤ የዩኒቨርሲቲው አስተዳደር ተማሪዎቹ የአለም የትምህርት አሰጣጥ በደረሰበት ደረጃ እንደሉ ያምናል።ተማሪያቹ ግን የዩኒቨርስቲ ደረጃ ሊያስመድባቸው የሚችል ምንም መለኪያ የለም።

የአሜሪካ የሕግ ተማሪዎች በቅድሚያ በሌላ ትምህርት የተመረቁ ናቸው። የትምህርት አሰጣጡ በጣም ከባድ ነው ተማሪዎች በርካታ የሕግ ነክ ጉዳዮችንና ውሎችን በያንዳንዱ ማታ ማንበብ አለባቸው። እነዚህም በመቶ በሚቆጠሩ ገጾችን የሚያጠቃልሉ ናቸው። ከመደበኛ ክፍል ውጭ የአሜሪካ ተማሪዎች በሕግ ግምገማና ክለሳ፤ በፍርድ የችግር አፈታት ሂደት፤ የደንበኖች አገልግሎት ምክር በመሳሰሉት ከሕግ ትምህርት ቤት ውጭ መስተፍ አለባቸው፤ ተማሪዎች ለበርካታ ሰዓታት የሕግ የቢሮ ፀሃፊ ሆነው መስራት ይጠበቅባቸዋል።

*አብርሃ በላይ:* በጅሪስት መጣጥፍው ላይ እንደገለፁት ተማሪዎች የሰሩትን ለመንግስት እንዳያሳዩ መለመነወትን በተመለከተ ጽፈዋል፤ በመጀመሪያ የተሰማዎት ምንድን ነበር? ተማሪዎቹ ለምን እንደሰጉ ጠይቀዋቸዋል? እርስዎስ አሳልፈው እንደማይሰጡ አረጋግጠውላቸዋል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : ይህንን ጥያቄ ሳነበው በጣም ደነገጥኩ የመጀመሪያውን ሳየው የተሸከምኩትን ወረቀት ጥየ ስለሁኔታው ማሰላሰል ጀመርኩ። በመቀጠል ምን ማድረግ እንደሚገባ እስከማስብ እስከ ቀጣዩ ቀን ወረቀቶቹን ማረሜን ቀጠልኩ በዚሁ ሂደት በርካታ መረጃዎች የያዙ ወረቀቶች አገኘሁ። ምን ማድረግ እንዳለብኝ ማወቅ ተሳነኝ፤ ነገር ግን ክፍል ከመግባቴ በፊት ተማሪዎቹን ምንም ስጋት እንዳያድርባቸው ነገርኩአቸው። እንዲያውም ስለሚያሳስባቸው ጉዳይ እንዲናገሩ አበረታታኋቸው ።ሆኖም ምንም አልተናገሩም። በንባብ ክፍለ ጊዜ ውስጥ በክፍሉ ውስጥ ለ15 ደቂቃ ጠቅላላ ዝምታ በሰፈነበት ሁኔታ ቆምኩ። የነበረኝ ግምትም ከመካከላቸው አንዱ ሰው ይናገረል የሚል ነበር። ማንም ምንም መረጃ ማቅረብ አልቻለም። በመሆኑም ምንም ነገር እንዳልተፈጠረ ዝም ብዬ ማስተማር መቀጠል ነበረብኝ ከዚያ ቀን በኃላ ማንም ተማሪ በግሉ የአነጋገረኝ የለም።

*አብርሃ በላይ:-* የእርሰዎ ግምት ተማረዎች ብቻ መናገር ይፈራሉ የሚል ነው ወይስ በግል ጭውውት እንደተገነዘቡት በፖለቲካና ወሳኝ በሆኑ ጉዳዮች መምህራንም ተመሳሳይ ፍራቻ አለባቸው?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* :- ከአተዳዳሪዎቹና ከመምህራን በግልፅ የሚነገረው ሁሉም ሰው የሚሰማውን ለመናገረ ነፃ ነው የሚል ነው። ስለፎረም አስተያየት መፃፌን ለሁሉም ተናግሬአለሁ፤ አንዳቸውም ግን ጥሩ አይደለም አላሉኝም። እንዲያውም ሌላ መምህር በመተርጎም ተባብሮኛል። ተቋሙ መምህራን ጥናታዊ ወረቀቶች የሚያቀርቡበት አልፎ አልፎ የምርምር ቀናትን ያዘጋጃል። ውይይቶቹ አልፎ አልፎ ሞቅ ያሉ ናቸው። በእነዚህ አይነቶች ዝግጅቶች በአንዱ ንግግር አድርጌአለሁ መምህራንም ዝግጅት አቅራቢዎችን በግልፅ ይጠይቃሉ።

*አብርሃ በላይ* :- በፃፉት የጅሪስት አርቲክል ላይ "የተወሰኑ ተማሪዎች በምንም ረገድ እውነተኛ ሀሳባቸውን ለኢትዮጵያ መምህራን እንደማይነግሩ ምክንያቱም ጉዳዩ ወደ መንግስት ጆሮ ይደርስና ቅጣት ያስከትላል የሚል ስጋት ስለአለባቸው ነው። ሌሎቹ ወረቀታቸውን ወደ አሜሪካ ወንድወስደው ለምነውኛል። ከዚያም በግቢው ምን እየተከናወነ እንደሆነ ሕዝብ ያውቀዋል" ሲሉ ጠይቀዋል በዚህ ረገድ የእርሰዎ ተማረዎች ለትምህርቱ ብቻ እንጅ ለወሳኝ ጉዳዮች ያልፈለጉት በዚህ ምክንያት ነው የሚል ስሜት አሳድሮበወታል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* : ቀደም ሲል ለመግለፅ እንደሞከርኩት ተማሪዎች ማንኛውንም ወሳኝ የአስተሳሰብ ውይይት መሳተፍ አይፈልጉም። የተሰጣቸው መረጃ ሳያብላሉ፤ የመልክቱን ውስጠ ባህሪ ሳይረዱ ዝም ብለው ማጥናት ብቻ ነው የሚሹት። ይህ አይነት የአምሮ ዝግጅት ከፍራቻ የመነጨ ሊሆን ይችላል፡ ወይም ቀደም ሲል የተማሩበት ስልት ሊሆን ይችላል። እኔ አላውቅም፤ የክፍል ውይይት የሚባል አይካሄድም፤ ተማሪዎችም ዝግጁ አይደሉም። ኢትዮጵያ ውስጥ በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ሳይሆን በሌላ የሙያ መስክ ለማስተማር የመጡ ጓደኞችና አንዳንድ ኢትዮጵያውያን እንደነገሩኝ ባህሉ እራሱ ሰዎች እንዲናገሩ የሚያበረታታ አለመሆኑን ነው።

አሜሪካዊ መምህር ከሚያስተዳድረው የእንግሊዘኛ ቋንቋ ት/ቤት ተጋባዥ መምህር ሁኜ በተደጋጋሚ ተገኝቻለሁ። እድሜአቸው ከ **10-17** ዓመት የሆኑ ታዳጊ ወጣቶች በጣም የሚያስገርም የተለያዩ ጥያቂዎች በመረጃ መልክ እንድሰጣቸው ሲጠይቁም እኔ በጣም ተቸግሬ ነበር። ከክፍል ከወጣሁም በኃላ በመንገድ ተከትለው በርካታ ጥያቄዎችን እድመልስላቸው ለምነውኛል። እነዚህ በእንግለዚኛ ቋንቋ ችሎታቸው ብቻ ሳይሆን በአስተሳሰባቸውም እኔ ከማስተምራቸው የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች በጣም የላቁ ናቸው። ይህ ለመማር ያላቸውን ፍላጎትና ብስለትም የጨመረ ነው። ይህ ነው የእኔ ልምድ ይህን ስለአመጣው ልዩነት ግን ልነግርህ አልችልም።

*አብርሃ በላይ* ፡- እንደጠቀሱልኝ የቋንቋ ችግርም እንዳለ ነው በእንግሊዘኛ ቋንቋ ሕግ እያስተማሩም ነው፤ የሕግ፡ ቋንቋ እራሱ ለአንድ ተራ ሰው በጣም ተፈታታኝ ነው። በዚህ ረገድ የሕግን ፅንሰ ሀሳብና መርህ ለመረዳት የቋንቋው ችግር ተፅዕኖ ያደረገባቸው ይመስለወታል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡- የሕግ ቃላት ለእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪውም የውጭ ቋንቋ ነው የሚመስሉት። የአሜሪካ ተማሪዎች ወደ ሕግ ትምህርት ቤት ሲገቡ ሁሉንም የሚነገረውን ነገር ሁሉ ይረዳሉ ማለት አይደለም። ከኢትዮጵያ ተማሪዎች በርካታ መልስ ያልተሰጠባቸው የፈተና ወረቀቶች አገኛለሁ። በዚህ የተነሳ አማርኛ መማር የጀመርኩት ሁል ጊዜ "ገብቷችኃል፤ ግልፅ ነው" እና "ጥያቄ አላችሁ" በማለት በአማርኛ እጠይቃለሁ። የአማርኛ ቃላቶችን ብትመለከት ክፍል ውስጥ ያለውን ሁኔታ ምን ያህል ዝቅ ያለ መሆኑን ልትመዝነው ትችላለህ። ተማሪዎቹ እንግሊዝኛ ስለማይናገሩ የዩኒቨርስቲ ደረጃ በጠበቀ ሁኔታ ለማስተማር በጣም ችግር ነው። በጣም ጥሩ የሚባሉ መምህራን ምንም የሚያመጡት ልዮነት የለም። የሚገርመው የኑቨርስቲው እንግሊዝኛ ብቻ መጠቀምን ይመርጣል፡ ሁሉም የውጭ መምህራን እንደሚያውቁት በርካታ ክፍሎች በአማርኛ ነው የሚያስተምሩት። ተማሪዎቹ የምናስተምረውን እያንዳዱን ቃል እየፈታን እንድንነግራቸውና ምን እንደተነገረ እንዲገባቸው ይፈልጋሉ። ጥቂቶቹ ኢትጵያዊ መምህራንም በጣም የሚዘወተር፡ ንግግር እንኳ ሳይቀር ከእኔ ጋር በእንግሊዝኛ ቋንቋ ማድረግ ይሳናቸዋል። በመሆኑም ክፍል የሚያስተምሩት በአማርኛ እንደሆነ ጥርጥር የለኝም። ሁሉ የተቋሙ መግባቢያ ቋንቋ የሚፃፈው በአማርኛ ነው በመሆኑም ማስተርጎም አለብኝ። ስብሰባዎችን ለመሳተፍ የሚያሳስብሽ ነገር የለም ተብሎ ተነግሮኛል። ምክንያቱም ተሰብሳቢዎቹ የሚነጋገሩት አማርኛ ወይም ትግርኛ ነው። በዚህ የተነሳ ብዙ ነገሮች አምልጠውኛል። ብቸኛው ቃል ጉባኤ የማነበው የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማህበር ነበር። እነርሱ ወደ እንግሊዝኛ ለእኔ አስተርጉመው ይሰጡኛል በዚህም የእኔን ቋንቋ አለመቻል አስተናገዱ በማለት እንቀላለዳለን።

*አብርሃ በላይ* ፡- የሕግ ትምህርት ቤቱ በቂ የሆነ የሕግ ትምህርት የሚሰጥበት በመቀረፀ ድምፅ የታገዘ ቤተመፃህፍት አላቸው?

*አቢጌል ሳሊስቡሪ* ፡ መፃህፍት ቤቱ በጣም ትንሽና እርዳታ የሚሻው ነው። የሕግ ትምህርት ቤቱ አዲስ ሕንፃ ተገንብቶለታል፡ ነገር ግን መፃህፍት፤ ቁሳቁሶች (ወንበር፤ መረጃዛ፤ የመሳሰሉት) እና ኮምቢተር ያስፈልገዋል። የአሜሪካ ቤተመፃህፍት በጣም ትላልቅ ናቸው፤ ምክንያቱም የሕግ ባለሙያዎቹ ስለአለፉ የሕግ ውሳኔዎች መረጃ ማግኘት አለባቸው። የአሜሪካ ሕግ መሰረት የሚያደርገው በአብዛኛው በተላለፉ የሕግ ውሳዎች በመሆኑ የሕግ ሰዎች ያለፉትን ወደ ኃላ ተመልሰው የማየት ግዴታ አለማቸው። የኢትዮጵያ ሕግ ደግሞ በሕግ በተደነገጉ ጉዳዮች ላይ የተመሰረተ ነው በመሆኑም የሕግ ባለሙያዎቹ ደግሞ በሕጉ የተደነገገውን ማዛመድ ብቻ ነው የሚጠይቃቸው። ይህም ሆኖ የመቀሌ ዩኒቨርስቲ ቤተመፃህፍት ማደግ አለበት። የአውሮፓ ሕብረት በሰጠው ልገሳ ጥቂት አዳዲስ መፃህፍት ገብተዋል። ሆኖም ገና ብዙ ያስፈልጋቸዋል፡ ኮምፒተርና የኢንተርኔት ግንኙነት ሌላው ጉዳይ ነው። ተማሪዎቹ ይቅርና መምህራን እንኳ ጥቂት ብቻ ናቸው ይህን፡ የሚጠቀሙት።

*አብርሃ በላይ* ፡- የመንግስት ወገኖች እንደሚከሱት እርሰዎ ተማሪዎቹን **HR 2003** እንዲቀበሉ ገፋፍተዋል ይላሉ? እውነት ተማሪዎቹ ላይ ተፅዕኖ አሳድረዋል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡ እንዲህ አይነት አስተያየት የሚያሳዝን ነው የእኔ ማስተማሪያ እንደሚለው ተማሪዎቹ ሀሳባቸውን መግለፅ ነፃነት አላቸው ይላል። በዚህም አንዱ ያንዱን አመለካከት ማክበር አለበት እነርሱ በእኔ ሀሳብ አለመስማማት ይችላሉ፤ ለክፍሌ ተማሪዎች በየሳምንቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ አስተሳሰባቸውን እንዲገልጹ ፈተና እሰጣቸዋለሁ።ለፈተናው

ደረጃም የምሰጣቸው እንዴት እንደሚያስቡ እንጂ ምን ሊያስቡ ይችላሉ ብዬ አይደለም። ስለ **HR 2003** የተነጋገርኩት በአንድ ክፍለ ጊዜ ብቻ ነው። በእርግጥ አንድ ተማሪ እኔ ስለአለኝ አስተያየት ጠይቆኛል። ይህን አጋጣሚ ተጠቅሜ ስለምጣኔ ሀብት ማዕቀብ ውጤታማነት ጠይቄአለሁ፤ ተማሪዎቹም ለእነርሱ የሚመቻቸውን እንዲያስቡ አበረታትቻለሁ፡ እኔ እንደማስበው ለተወሰነ ጊዜ እኔን ያናገረኝ ሁሉ እንደሚረዳው ይህ አይነት ክስ ከእኔ መልካም አመለካከት ውጭ ነው።

*አብርሃ በላይ* ፡ የሚያስተምሩትየሰብአዊ መብት ሕግ ነው አሁን የተገነዘቡትንና ባነበቡት የአለማቀፍ የሰብአዊ መብት ስለ ሕግ የበላይነት ዘገባና እርሰወ ከሚያስተምሩት ሰብአዊ መብት ትምህርት ጋር እንዴት ያገናኙታል?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡- በኢትዮጵያ ውስጥ በተጨባጭ ያለው የሰብአዊ መብቶች ሁኔታ ካየሁ በኃላ መንግስት ስለሰብአዊ መብቶች በዩኒቨርስቲዎች እንዲሰጥ ማድረጉ አስደነገጠኝ። ለተማሪዎቹ ሁል ጊዜ የምነግራቸውና በተደጋጋሚ፡ ስለአሜሪካ የማነሳው ነገሮችን ለማብራራት በሚል ነው፡ አሜሪካን በምሳሌ እጠቅሳለሁ ምክንያቱም በጣም የማወቀው አሜሪካን ስለሆነ እንጂ፤ አሜሪካ በጣም ትክክል ነው በሚል አይደለም። ማንኛውም ሀገር የአለማቀፍን የሰብአዊ መብት መርህ በሙሉ ገቢራዊ የሚያደርግ የለም፤ ዋናው ጠቃሚ ጉዳይና ቁም ነገርወደ ዋናው የመብት መከበር ለማምጣት በሌሎች ሀገራትም ላይ ተደጋጋሚ ግፊት ማድረግ ነው።

*አብርሃ በላይ* ፡ የእርሰዎን የስራ መቀጠር የአመቻቸው ድርጅት ላይ ምን የተፈጠረ ይመስለወታል? እርሰዎስ ሌሎች የአሜሪካ መምህራን ኢትዮጵያ ውስጥ እንዲያስተምሩ ይረዳሉ?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡ ለአሁኑ ብዙ ሰዎች ወደ ኢትዮጵያ ባይላኩ ይሻላል። አሁን በቅርብ **200** አመልካቶች መካከል ጥቂት ግለሰቦች በመጭው ጥቅምት ላይ ለመሄድ እንደተመረጡ አወቃለሁ። ስለፕሮግራሙ በጣም አሳሳቢ ጉዳይ አለኝ፡ ወደ ኢትዮጵያ ባለፈው አመት ከመሄዴ በፊት ሊነገሩኝ የሚገቡ ጉዳዮችን በዝርዝር መረጃ ይዥለሁ፤ ይህ መረጃ ቀጣዮቹ መምህራን ከመሄዳቸው በፊት እንዲደርሳቸው ይደረጋል። እንደ እኔ ግምት ብዙ ችግር እንዳይገጥማቸው ይረዳቸዋ የሚል ተሰፋ አለኝ። ዋናው የአሜሪካውያን ችግር ስለኢትዮጵያ ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎች አለማወቃቸው ነው። ከሀገሬ ከመልቀቄ በፊት መረጃ ለማግኘት ሞክሬ አለሁ።አጥጋቢ መረጃ ግን ማግኘት አልቻልኩም። ወደ ኢትዮጵያ ሌሎች እንዳይሄዱ እንቅፋት አልሆንም። ምክንያቱም አስተሳሰቤን ለመለወጥ በጣም የሚደንቅ ልምድ ነው ያገኘሁት።

*አብርሃ በላይ* ፡- የሚያስከትለውን መዘዝ ቢረዱ ኑሮ ይህን መጣጥፍ በጁሪስት ላይ ይጽፉ ነበር?

*አቢጌል ሳሊስበሪ* ፡ይህ በጣም ከባድ ጥያቄ ነው። ይህን ፅሁፍ ስጽፍ በጣም ችግር ያለበት ነገር እንደፃፍኩ አወቄአለሁ፡ ሆኖም ኢትዮጵያ ውስጥ ማንም ያውቀዋል የሚል ግምት ግን አልነበረኝም። ከዚህ በፊት ለጁሪስት ፅፌአለሁ የእኔ ስራ ግን ብዙ ሰዎችን አልሳበም ነበር፤ ስለኢትዮጵያ የፃፍኩት አንዳንድ መታወቅ ያለባቸው መረጃዎችን ለመስጠት እንጂ ለምንም ነገር አይደለም በፅሁፍ ላይ ስለተሰጠው ትኩረት አበሳጭቶኛል በመፃፌ ግን ብርቱ ስራ መስራቴ አስደስቶኛል።

*አብርሃ በላይ፡-* በዚህ ጉዳይ ላይ እኛ ጋር ለመነጋገር ጊዜዎትን ስለሰጡን በኢትዮሚዲያ ስም በጣም አመስግናለሁ፡ በግሌም ልምደወትንና ሀሳበወትን ስለ አካፈሉን ምስጋናየ የላቀ ነው።

*አቢጌል ሰሊስብሪ፡* -እኔም አመሰግናለሁ።